

# አባ በዝብዝ ካሳ- 2ኛ አጼ ዮሐንስ

ወንድወሰን ሰብስቤ

የኢትዮጲያ አካል ትግራይ ተናገሪ
እንዴት በቀሉብሽ እኒህ አሳፋሪ
ተልካሻ ትውልዶች የሙት ስብርባሪ
እንዴት ወጡ ካንቺ እነዚህ ቀፋፊ
አንቺን ሊነጥሉ ታሪክሽን ሻፋፊ
ከምን ወጡ ካንቺ እነዚህ እዳፊ
ዮሀንስ ተነስተህ አገርን ብታየው
ከንቱ ሆነ ዛሬ ደምህ የፈሰሰው
ውሉ ቁዋጠሮህን ጎጠኛ ሲያፈርሰው
ከቶ ምን ተሰማህ አገርን ሲቆርሰው
ጣሊያን የጣለው ጦቢያ ምድር
ችግኙ በቀለ ሲውል ሲያድር
መርገምት ተክል ሆነ አገር ሊሰብር
አንገቱን የሰጠው  እናቱን ያለው
ለክልል አልነበር አንገት የሰጠው
መተማ ላይ ነበር ደሙ የፈሰሰው
የባንዳ ልጅ መጣ ክደት የገባው
የመተማን ስራ ቸለል አረገው
መተማ ተናገር የዮሐንስ ደም
ታሪክ ይወቅሰናል ታሪክ ሲጣመም
ከንቱ ሆነ ደሙ ለምን ይባል ዝም
አባ በዝብዝ ካሳ የትግራይ አንበሳ
ገደል ይገባሉ አንተ ብትነሳ
ለምን ዝም ይባላል ቀስቅሱት ይነሳ
የመተማው ጀግና አባ በዝብዝ ካሳ
ታሪክህ ሲጠፋ ለምን ዝም ይባላል
ትግራይን ሊቆርጡ ከኢትዮጲያ አካል
መቃብሩ ይከፈት ተናገር ዝም አትበል
ይውለብለብ ታሪከህ ባንዲራህ ይሰቀል
ጉድክን አላየነው በምድርህ ሲቃጠል
ትግራዮች ተነሱ ትግሉን አቀጣጥሉ
ኢትዮጲያን የካዱ ማፋን እስከሚሉ
ፍትህን እንዲያውቁ ሰውን የገደሉ
የዮንስን ደም ያቀለሉ ሁሉ
ፍትህ ፊት ይቁሙ ቅጣት ይቀበሉ
የዮሐንስ ዘሮች አረ ዝም አትበሉ
የአሉላ አባ ነጋ የዮሐንስ ዘር
ምን እያረጉ ነው ሀገር ሲደፈር
አሳይቶን ነበር የሀገር ድንበር
ስሙ እንዳይነሳ ባንዳው ሲያብር
ጀግናው ዝም አትበል ያስገባል ከዱር
ጦቢያ እየጠፋች እንዴት ይታደር
የዮሐንስ ልጆች ዝም አትበል ተነሱ
የአሉላ አባ ነጋ ውሀ አጣ ፈረሱ
ተነሱ አስከብሩ ባንዳውን ደምሥሱ
ሊለዮህ እያሰቡ አጥሩን ሲያጥሩ
የጀግኖች ሀገር ነች በሉ ተናገሩ
የወያኔን አጥር ተነሱ ስበሩ
አሻፈረኝ ካሉ ዮሐንስን ጥሩ
ለመንደር አይደለም ዮሐንስ የሞተው
ለክልል አይደለም አንገቱን የሰጠው
ደሙ ይከስህል መተማ የፈሰሰው::